# የትምህርት ቤት COVID-19 ምርመራ ስምምነት ቅጽ

**የትምህርት ቤቱ የጤና አገልግሎቶች ፕሮግራም** (SHSP) **ልጅዎን ለ COVID-19 ለመመርመር** እና የተሰበሰበ ዉህድን ከሚመለከተው ባለስልጣናት ጋር ለማጋራት **እንዲሆን የእርስዎን ፈቃድ ለመቀበል ይህንን ቅጽ እየተጠቀመ ነው።** ምልክቶች፣ ምርመራ፣ እና የኮሮናቫይረስ ምላሽ ላይ ተጨማሪ መረጃ በ cdc.gov/coronavirus መገኘት ይችላል። የኮሮናቫይረስ ምልክቶች እና የ DC ምላሽ ላይ ተጨማሪ መረጃ በ www.coronavirus.dc.govመገኘት ይችላል። ለ በአካል መማር ትምህርት ቤቶችን ክፍት አድርጎ ማቆየት የ COVID-19 ስርጭት መከላከል ዉስጥ ትጉህ እንደምንሆን ይጠይቃል። በትምህርት ቤት ምርመራ ማድረግ ተማሪዎች እና ማህበረሰብ ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ የማድረግ አስፈላጊ አካል ነው።

**ልጄን ምን ያህል ደጋግመው ይመረምራሉ?**

ተማሪ ትምህርት ቤት ዉስጥ እያለ/ች መስፈርት የሚያሟሉ ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ተማሪው/ሯ ከትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያዎች የ COVID-19 ምርመራን ይቀበላል/ትቀበላለች **ስምምነት ላይ ተደርሶ ካለ።**

**ምርመራው ምንድነው?**

**ከተስማሙ፣** ልጅዎ ለ COVID-19 ቫይረስ ነፃ የህክምና ምርመራን ይቀበላል/ትቀበላለች። **የተያያዙ ሰነዶች ጥቅም ላይ መዋል ስለሚችሉ ምርመራዎች ተጨማሪ መረጃን ያቀርባሉ።** ለምርመራ ናሙናዎችን መውሰድ ትንሽ የመጥረጊያ መሳሪያን፣ የ Q-Tip የሚመስል፣ የአፍንጫ ፊት ለፊት በኩል ሁለቱም የአፍንጫ ቀዳዳዎች ዉስጥ መክተትን ይጠይቃል። ይህ ምርመራ በ COVID-19 የተጠረጠሩ እና ምልክቶችን ያዩ ግለሰቦች ላይ ምልክቶቹ ከጀመሩ ሰባት ቀናት ዉስጥ ይደረጋል።

**ስለ ምርመራው ዉጤቶች እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

ልጅዎ በትምህርት ቤት ምርመራ የሚሆን ናሙና ሰጥቶ/ታ ከሆነ፣ የትምህርት ቤቱ የጤና መኮንን (ነርስ) ከምርመራው ዉጤቶች ጋር በስልክ ያገኝዎታል። እንዲሁም እርስዎን ለማሳወቅ መረጃን ከተመሪው/ሯ ጋር ወደ ቤት እንልካለን።

**የልጄን የምርመራ ዉጤቶችን ስቅበል ምን ማድረግ አለብኝ?**

የልጅዎ ምርመራ ዉጤቶች ፖዘቲቭ ከሆኑ፣ የምርመራ ዉጤቶችን ለመገምገም እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለመነጋገር እባክዎ በአስቸኳይ የልጅዎ ሀኪምን ያግኙ። ልጅዎን ቤት ዉስጥ ማቆየት አለብዎት እና ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን ይከተሉ። የልጅዎ የምርመራ ዉጤቶች ኔገቲቭ ከሆኑ፣ ይህ ማለት ቫይረሱ የልጅዎ ናሙና ዉስጥ አልታየም ማለት ነው። ምርመራዎች **አንድ አንድ ጊዜ** ትክክል ያልሆኑ ኔገቲቭ ዉጤቶችን (“የዉሸት ኔገቲቮች” ተብለው ይጠራሉ) COVID-19 ያለባቸው ሰዎች ዉስጥ ያሳያሉ። ልጅዎ በመጀመሪያው ምርመራ ኔገቲቭ ከሆነ/ች፣ ሁለተኛ የማረጋገጫ ምርመራ በትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያዎች ይፈፀማል። ከሁለተኛ ምርመራ የሚገኙ ዉጤቶች በአጠቃላይ 2-4 ቀናት ዉስጥ በትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያዎች ይቀርባሉ። ሁሉም ተማሪዎች ከመመርመራቸው በኋላ ወደ ቤት ይላካሉ፣ የመጀመሪያው ምርመራ ዉጤቶች ምንም ቢሆኑ።

ከዚህ ቅጽ የሚገኙ ዉህድ እና የምርመራው ዉጤቶች እንደ COVID-19 ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች ይሰበሰባሉ እና ምናልባት ከሚመለከታቸው የትምህርት ቤትና የጤና ባለስልጣናት ጋር ሊጋሩ ይችላሉ።

<table>
<tr><th colspan="7">የግንኙነት መረጃ | በ ቤተሰብ/ሞግዚት/ተማሪ ( 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ) ይሞላል።</th></tr>
<tr><td>የተማሪ የአያት ስም፥</td><td colspan="4">የተማሪ የመጠሪያ ስም፥</td><td colspan="2">የትውልድ ቀን፥</td></tr>
<tr><td colspan="4">የትምህርት ቤት ስም፣</td><td colspan="3">ዋርድ፥</td></tr>
<tr><td colspan="2">የቤት አድራሻ፥</td><td>አፐት/አፓርት መንት፥</td><td>ከተማ፥</td><td colspan="2">ስቴት፥</td><td>ZIP/ዚፕ ኮድ፥</td></tr>
<tr><td colspan="3">የወላጅ/ የሞግዚት ስም፥</td><td colspan="4">የወላጅ/ የሞግዚት ስልክ፥</td></tr>
<tr><td colspan="3">በድንገተኛ ጊዜ የሚጠራ ሰው ስም፥</td><td colspan="4">በድንገተኛ ጊዜ የሚጠራ ሰው ስልክ፥</td></tr>
</table>

በጀርባዉ ቀጥሏል።

ከዚህ በታች በመፈረም፣ ከዚህ በታች ያሉትን አረጋግጣለሁ፥

- ይህንን ቅጽ በነፃነት እና በፍላጎት ፈርሜያለሁ፣ እና ከላይ ለተገለጸው ልጅ ዉሳኔዎችን ለማድረግ ሕጋዊ ስልጣን አለኝ።
- ልጄ አስፈላጊ ሲሆን ለ COVID-19 እንዲመረመር/እንዲትመረመር እስማማለሁ።
- ይህ ስምምነት እስከ ሴፕቴምበር 30፣ 2021 ህጋዊ, ተቀባይነት እንዳለው እረዳለሁ፣ ስምምነቴን እንዳነሳሁት ከልጄ ትምህርት ቤት ለተሰየመ ሰው በጽሁፍ ካሳወቅኩት በስተቀር።
- የልጄ ምርመራ ዉጤቶች እና ሌላ መረጃ በህግ እንደተፈቀደው ይፋ ሊደረጉ እንደሚችሉ እረዳለሁ።
- ዕድሜዬ 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆንኩኝ ተማሪ ከሆንኩ, ወይም ለራሴ የጤና እንክብካቤ በህግ ከተስማማሁ፣

ወደ እኔ የተላከ"የእኔ ልጅ" ማጣቀሻዎች መሰረት እና ይህንን ቅጽ ራሴን ወክዬ ሊፈርም እንደሚችል እረዳለሁ።

- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ ለድርጊቶች ወይም ግድፈቶች፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ የታሰበበት ጥፋቶች፣ ከባድ ቸልተኝነት፣ ወይም ሆን ተብሎ መጥፎ ምግባር ካልሆነ በስተቀር፣ ከሲቪል ተጠያቂነት ነፃ እንደሚሆኑ እረዳለሁ እንዲሁም እስማማለሁ።
- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ ከካምፓስ ላይ ክትትል የተነሳ የተለየ ተማሪ በቫይረስ ለመያዙ ተጠያቂ ተደርገው ሊወሰዱ እንደማይችሉ እረዳለሁ።

**ቤተሰብ/ሞግዚት/ተማሪ ( 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ) ፊርማ፥** ______________________________ **ቀን፥** ____________

| ለቢሮ ሥራ ብቻ | በትምህርት ቤት ሬጅስትራር እና የትምህርት ቤት ነርስ የተቀበለ የስምምነት ቅጽ |
|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| የሬጅስትራር ቢሮ ስም፥ | ፊርማ፥ | ቀን፥ |
| የነርስ ስም፥ | ፊርማ፥ | ቀን፥ |

**ይህ ቅጽ ተሞልቶ ካለቀ በኋላ ወደ ትምህርት ቤቱ የሬጅስትራር ቢሮ መግባት አለበት።**

**ለቢሮ ሥራ ብቻ፥** ሬጅስትርራሩ ሁሉም የተሟሉ የስምምነት ቅጾችን ሰንዱ እንደደረሰ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያ ማስገባት አለበት።

**መረጃ ለቤተሰቦች፣ ሞግዚቶች፣ እና ተማሪዎች**

ከ COVID-19 ጋር የሚያያዙ ምልክቶችን የሚያሳይ ተማሪ ክፍል ዉስጥ እንዲቆይ አይፈቀድለትም። እንሱ ወደ ተሰየመለት ለብቻ የመቀመጥ ክፍል ይወሰዳሉ እና ለ COVID-19 ምርመራ ለመገምገም ከትምህርት ቤቱ የጤና ነርስ ወይም የጤና ባለሙያ ጋር ይገናኛሉ። በፋይል ላይ የስምምነት ቅጽ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ለብቻ መቀመጥ ክፍል ይወሰዱ እና ወደ ቤት ለመሄድ የትምህርት ቤቱ አካሄዶችን ይከተላሉ።

- የስምምነት ቅጽን ለሞሉ እና ምልክቶችን ላሳዩ ተማሪዎች ምርመራ ይቀርባል።
- ተማሪው መስፈርቶችን ካሟላ/ች፣ ፈጣን ምርመራ ይደረግለታል/ላታል። ይህ ምርመራ በአፍንጫ መጥረጊያ መሳሪያ ይደረጋል እንዲሁም ዉጤቶቹ በ15 ደቂቃዎች ዉስጥ ይቀርባል። ዉጤቶቹ ለተማሪው/ዋ ከብካቢ፣ እና የትምህርት ቤት አመራር(ች) ይነገራል።
  - የምርመራው ዉጤቶች **ፖዘቲቭ** ከሆኑ፣ ተማሪው/ዋ ፖዘቲቭ እና ማስተላለፍ እንደምችል/ትችል ይታሰባል። ዉጤቶቹ ወዲያው እንደወጡ ለተማሪ፣ ቤተሰብ፣ እና የተማሪ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ይነገራሉ። ተማሪው/ዋ በእንክብካቤ ሰጪ እስከሚወሰድ/ሚትወሰድ ድረስ የሚቆጣጠር ለብቻ መቀመጥ ክፍል ዉስጥ ይቆያል/ትቆያለች። ማንኛዉም ሊያጋጥም የሚችል የቅርብ ንክኪን ለማስወገድ ትምህርት ቤቱ እንዲያዉቅ ይደረጋል።
  - የምርመራው ዉጤት **ነገቲቭ** ከሆነ፣ ሁለተኛ የማረጋገጫ የአፍንጫ መጥረግ ምርመራ PCR (ፖሊሜሬስ ቼይን ሪያክሽን) የምባለው በትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያ ይደረጋል። ተማሪው/ዋ በእንክብካቤ ሰጪ እስከሚወሰድ/ሚትወሰድ ድረስ የሚቆጣጠር ለብቻ መቀመጥ ክፍል ዉስጥ ይቆያል/ትቆያለች። በትምህርት ቤቱ የጤና ባለሙያ የተሰበሰበው ናሙና ከካምፓስ ዉጭ ወዳለው የምርመራ ማዕከል ለምርመራ ይላካል። የ PCR ምርመራ ዉጤቶች ከ2-4 ቀናት ዉስጥ ከተወሰዱ በኋላ ለተማሪ ቤተሰብ ይላካሉ። ተማሪው/ዋ የPCR ምርመራ ውጤቶች እና የተቋቋሙ የትምህርት ቤት ፕሮቶኮሎች መሰረት ወደ ክፍል ለመመለስ የሚፈቀድለት/ላት ይሆናል።
- የምርመራ ውጤቶቹ እንዳስፈላግነቱ ከትምህርት ቤቱ፣ DC ጤና፣ ወይም ሌሎች የአካባቢው እና የፌዴራል የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ጋር ሊጋሩ ይችላሉ።
- በቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ሕግ (FERPA) እና አካባቢ ግላዊነት ጥበቃዎች መሰረት፣ የተማሪው/ዋ በግል ደረጃ መለየት የሚችል መረጃ በፍጹም ለህዝብ ይፋ አይሆንም። ሁሉም መረጃ በምስጢር ተይዞ ይቆያል።
- CDC በ COVID-19 የተያዘ ማንኛዉም ሰው ምልክቶችን ካየ በኋላ፣ በምልክቶቹ ክብደት መሰረት፣ ለ10 እስከ 14 ቀናት ኳራንታይን ዉስጥ መቆየት እንዳለበት ይመክራል። አንድ ግለሰብ በ COVID-19 ተመርምሮ ፖዘቲቭ ከሆነ መከተል ያለበት መመሪያ ላይ ተጨማሪ መረጃ በ፥ https://coronavirus.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/coronavirus/page_content/attachments/6222020- COVID-19_DC_Health_Guidance_for_Persons_Test_Positive_for_COVID19.pdf. መገኘት ይችላል።

በሽታው ላይ እና የራስዎን እና ቤተሰብዎን ደህንነት ጠብቀው ለመቆየት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ኮሮናቫይረስ ድህረገጽን በ www.cdc.gov/coronavirus ይጎብኙ።

ወረርሽኙን ለመከላከል ዲስትሪክቱ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ኮሮናቫይረስ ድህረገጽን በ www.coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።

የትምህርት ቤትዎ COVID-19 ምላሽ መስጫ ጥረቶችን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና/ወይም የትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ቢሮን ያግኙ።

የኮሮናቫይረስ ምልክቶች

- 100.4 ወይም ከዚያ በላይ የሰዉነት ሙቀት/ቴምፕሬቸር
- ብርድ ብርድ ማለት
- ማሳል
- የትንፋሽ እጥረት ወይም ለመተንፈስ መቸገር
- ድካም
- የጡንቻ ወይም የአካል ህመም
- አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ችሎታ ማጣት
- የጉሮሮ ህመም
- መታፈን ወይም የአፍንጫ ፍሳሽ/ንፍጥ
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስታወክ
- ተቅማጥ
- በአጠቃላይ የጤንነት ማጣት ስሜት

ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌለው/ላት፣ አቅራቢን ለማግኘት፣ እባክዎ እዚህ ጋ የሚገኘዉን የ DC ሕፃናት ክትባት ቦታዎችን ይጎብኙ።